የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ ለዐቃብያነ ሕግ

ተስፋዬ አባተ አበበ (ዶ/ር)

ጎዳር 10-11/2016ዓ.ም.

አዲስ አበባ

- **አጠቃላይ ዓላማ፡**
- **ከዚህ ሥልጠና በኋላ ሠልጣኞች፡-**
- **የወንጀል ሥነ ሥርዓት ህግ ድንጋጌዎችን እንዲሁም ልዩ ትኩረት የሚሹ ባለጉዳዮችን ፍላጎትበመለየት እውቀታቸውንና ክህሎታቸውን በማሳደግ በሀገራችን ቀልጣፋና ውጤታማ የፍትህ ሥርዓት እንዲገነባ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያበረክታሉ።**

- **ዝርዝር ዓላማዎች፡በርዕሰ ሥልጠናው የተዘረዘሩትን ንዑሳን ርዕሶች ከሠለጠኑ በኋላ ሰልጣኞች፡-**

- ስለ ተከሳሽ መሰማትና መቅረብ ያለውን ሥነሥርዓት ይተረጉማሉ፣
- የዕምነት ክህደት ቃል አቀባበል ዘዴንይለያሉ፣
- ስለ ቅድመ ምርመራ ይተገብራሉ፣
- የክስ አሰማም ሂደት፣ በሂደቱም በተከራካሪ ወገኖች የዳኞችን ሚና ይለያሉ፣

- ጭብጥ የመመስረት ዘዴን ይለያሉ፣
- ውጤታማ የሆነ የቀጠሮ አሰጣጥ ዘዴን ይተነትናሉ፣
- የይግባኝ አሰማምና ቀጠሮ አሰጣጥ ዘዴን ልምድ ያዳብራሉ፣
- የወንጀል ተጠቂዎች፣ ህፃናትና ሌሎች ልዩ ትኩረት የሚሹ ባለጉዳዮችን ስለሚያስፈልጉ ልዩ ስነ ሥርዓቶች ይገልጻሉ፣

1) ስለቀዳሚ ምርመራ

- ቀዳሚ ምርመራ ለወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ያለው ጥቅም
- በኮመን ሎ ተጠርጣሪው በወንጀል እንዲከሰስ በቂ ማስረጃ መኖሩን ለማረጋገጥ ነው::
- በሌሎች- ማስረጃን ጠብቆ ለማቆየት ነው
- በኢትዮጵያ- ማስረጃን ጠብቆ ለማቆየት ተሚደረግ ጥንቃቄ ነው::

የዐ/ሕግ ሥልጣንና የፍ/ቤት ሚና

- በቀዳሚ ምርመራ የሚታዩ ጉዳዮች
- 1) ግዴታ- ከባድ የሰው ግድያ ቁ/539 እና የውንብድና ተግባር ቁ/671
- 2) በዐ/ሕግ ጥያቄ ጉዳዩ ወዲያውኑ በቀዳሚ ምርመራ ፍ/ቤት እንዲታይ-
- 2) በወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/38(ለ) -በዐ/ሕግ ውሳኔ ቀዳሚ ምርመራ ሊደረግ ይችላል
- በከፍተኛ ፍ/ቤት ሥልጣን ሥር በሚወድቁ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ብቻ

- የተከሳሹ ማንነት ተረጋግጦ ሂደቱ መጀመር አለበት
- የዐ/ሕግ ምስክሮች ይጠራሉ
- ማስረጃ መዝግቦ ለማቆየት ብቻ መሆኑ በፍ/ቤቱ መነገር አለበት::
- ተከሳሹ መስቀለኛ ጥያቄ መጠየቅ ይችላል፤
- የማጣሪያ ጥያቄ
- ፍ/ቤቱ ሌላ ምስክርም ጠርቶ መስማት ይችላል

- ተከሳሽ ቃሉን ሊሰጥ ይችላል
- ቃሉም በፍ/ቤቱ ተነብቦ በፍ/ቤቱ ይፈረምበታል።
- ምስክሮቹም ይመዘገቡለታል
- ይህም ሀሰተኛ ምስክር እንዳይቀርብ ይከላከላል።
- ግልባጩ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ሬጅስትራር ይላካል፤

- ዐ/ሕግና ተከሳሽ ግልባጩን ከከፍተኛው ፍ/ቤት ሬጅስትራር መውሰድ ይችላሉ::

ክስ አይቀርብም የማለት ውሳኔ

- ዐ/ሕግ ክስ ላለማቅረብ ሊወስን ይችላል፤
- **ምክንያቶችና አተገባበራቸው**
- በወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/42
- በቂ **ማስረጃ** ከሌለ
- የተከሰሰውን ሰው ለማግኘት ካልተቻለና በሌለበት የማይታይ ከሆነ
- በይርጋ ከታገደ፣
- ምሕረት ተደርጎ ከሆነ
- ሕ/መ/አ/ 28(1)- በይርጋ የማይታገዱ ወንጀሎች፤

ክስ አይቀርብም የማለት ውሳኔ ከምርመራ መዝጋት ጋር ያለው ልዩነት

- ክስ አይቀርብም- በይርጋና ምህረት ምክንያት ካልሆነ ለተከሳሹ መቃወሚያ አይሆንም::
- ተከሳሹ ሲገኝ፤
- በቂ ማስረጃ ሲገኝ- መክሰስ ይቻላል፤
- በቁ/39 መሠረት ምርመራ ሲዘጋ- ጊዚያዊ ከሆኑት በስተቀር መቃወሚያ ሊሆኑ ይችላሉ::

- በሞተ ሰው፣
- ተከሳሹ 9 ዓመት ያልሞላው ከሆነ፣ ክስ አይቀርብም፤
- ጊዜን በተመለከተ
- ክስ አላቀርብም ብሎ ለመወሰን- ምርመራ ካለቀ በኋላ፤
- መዝጋት- የምክንያቱ መኖር እንደተረጋገጠ፤
- ምርመራ ሳይጠናቀቅም ሊሆን ይችላል።

2) ክስ ስለማቅረብ

- ዐ/ሕግ የምርመራ መዝገብ በደረሰው በ15 ቀን ውስጥ ክስ ማዘጋጀት አለበት፤
- በወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/108-122 መሠረት ክሱን አዘጋጅቶ ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ማቅረብ አለበት፤

- አንዱ ወንጀል ሌላ ፍ/ቤት አንዱ ሌላው ዘንድ የሚቀርብ ቢሆን እንዴት ክስ ይዘጋጃል?
- ምሳሌ- በወ/ህ/ቁ/665 በስርቆት፣ በተጨማሪ በወ/ሕ/ቁ/854 ደንብ መተላለፍ ቢኖር
- 665- ፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት
- 854- የከተማ ፍ/ቤት ሥልጣን
- አንድ ላይ ይቀርባል።

የክስ አጻጻፍ

- የክሱ ይዘት- ከወ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 11(ሐ)-ጊዜ ምንን ያካትታል
- ጊዜ- ሠዓት፣ ቀን፣ ወርና ዓመትን ያጠቃልላል
- አንድንዶች ከክሱ ማስረጃ አንጻር መታየት አለበት ይላሉ።
- በወ/ህ/ቁ/23 መሠረት- ወንጀሉን የሚያቀቁሙትን የሕግ፣ ግዙፋዊና ሞራላዊ ክፍሎች ተማልተው መቅረብ አለበት። ወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/111

- በወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/112 መሠረት- ክሱ ወንጀሉንና ሁኔታውን ከሕጉ አነጋገር ጋር በጣም በተቀራረበ መልኩ መጻፍ አለበት፤
- ወንጀሉን የሚያከብድ ሁኔታዎች- ከሕጉ አንጻር፤
- ቀደም ሲል ለፈጸማቸው ምክያቶች ጥፋተኛ መሆኑ አይገለጽም፤

- ማስረጃ
- ዝርዝር
- ምን እንደሚያስረዳ መግለጽ- ጉምሩክ ዐ/ሕግ፤
- የጸረ ሙስና አዋጅ መሠረት- ማስረጃዎች የሚያስረዱትን ነገር ተዘርዝሮ ይቀርባል፤

3) ስለ ተከሳሽ መሰማትና መቅረብ

- የክስ ማመልከቻ የቀረበለት ፍ/ቤት ነገሩን ለማየት ሥልጣን እንዳለው ማረጋገጥ አለበት
- ከዚያም ክስ ይሰማል።
- የክስ ሂደት ተከሳሹ ጥፋተኛ ወይም ንጹሕ ስለመሆኑ የሚወሰንበት ስለሆነ ወሳኝ ነው።
- የባለሙያ ጥንቃቄንም ይሻል።

ክስ ለመስማት የሚደረጉ ዝግጅቶች

- ቀን መቁረጥና ተከራካሪዎችን ከነምስክሮቻቸው ስለመጥራት
- ፍ/ቤቱ ሥልጣን ያለው ከሆነ ክሱን የሚሰማበትን ቀን በመወሰን ቀጠሮ ይሰጣል።
- ተከሳሽ እንዲቀርብና መልስ እንዲሰጥ መጥሪያ ይላክለታል ቁ. 127
- የክሱ ቅጅ ከነሠነድ ማስረጃው ይላክለታል።

- ፍ/ቤቱ ቀን ሲወስን- ተከሳሹ የሚገኝበትን ቦታ ርቀት፣ ምስክሮች ለመቅረብ የሚወስድባቸውን ጊዜ፣ የፍ/ቤቱ የመዝገብ ብዛት ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው። ቁ. 123
- በአር ቲ ዲ በተባለው አሠራር- ክሱ ሲቀርብ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ይቀርባሉ፤
- ቀጠሮ መስጠት ሳያስፈልግ ክሱ ይሰማል።

- ዐ/ሕግና ተከሳሽ የምስክሮችን ዝርዝር ለሬጅስትራር ማቅረብ - ቁ. 124
- በፍ/ቤቱ ሬጅስትራር በኩል መጥሪያ ይላክላቸዋል።
- የተለመደው አሰራር ክሱ በሚሰማበት ቀን ባለጉዳዮች ምስክሮቻቸውን እንዲያቀርቡ ይታዘዛል
- በአሁኑ ወቅት አንደንድ ፍ/ቤቶች ግራ ቀኙ ምስክሮቻቸውን ይዘው እንዲቀርቡ ይታዘዛል።

ክስን ለተከሳሽ ስለማድረስ

- ክሱ ቀድሞ ለተከሳሽ ሊላክለት ይገባል ቁ. 109 (4) እና 94 (2) (ሰ)
- የተከሰሱ ሰዎች የክስ ቅጅ የማግኘት መብት አላቸው- ሕገ-መንግስት አ. 20(2)
- **ጥያቄ**
- ተከሳሽ ማስረጃን የሚያገኘውና የሚያየው መቸ ነው?

- የክስ ማመልከቻው ቅጅ ለተከሳሽ ሲላክለት ከማስረጃ ጋር ስለመሆኑ ሕጉ በግልጽ አያመለክትም::
- ስለሠነድ ማስረጃ ግልጽ ድንጋጌ የለም::
- ማስረጃው ለተከሳሽ ቢደርሰው- በቂ ጊዜ አግኝቶ ለመዘጋጀት ያስችለዋል፣

በቀጠሮ አለመገኘትና ውጤቱ

- ስለተከሳሽ አለመቅረብ
- ተከሳሽ መጥሪያ ደርሶት ካልቀረበ በእስር እንዲቀርብ ይታዘዛል ቁ. 125 እና 160 (2)
- መጥሪያ ካልደረሰው- የማይገኝ ከሆነ ምን ይደረጋል?
- አከራካሪ ነው::

- በቂ ባልሆነ ምክንያት ተከሳሽ ሳይቀርብ ከቀረ
- በሌለበት ይሰማል ቁ. 160-163
- ከ12ዓመት በማያንስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ከቁ. 343-354 ያሉትን ከፈጸመ
- በሌሎች ወንጀሎች ተከሳሽ በተገኘ ጊዜ እንዲቀጥል መዝገቡ ተዘግቶ እንዲቆይ ማድረግ፤

- ክሱ መታየት ጀምሮ የዐ/ሕግ ማስረጃ ሳይሰማ ተከሳሽ ከቀረ 161 (2) የተመለከቱትን ወንጀሎች በተመለከተ በሌለበት ይታያል።
- እንዲህ ዓይነት ወንጀሎች ከሌሉ ክሱ ይቋረጣል።

- የዐ/ሕግ ማስረጃ ከተሰማ በኃላ ቢቀርስ?

- **ዐ/ሕግ ካልቀረበ**
- **የሚሰጠው መፍትሔ የተለያየ ነው።**
- **አንዳንድ ቦታ መዝገቡን መዝጋት፤**
- **ሌሎች ቀጠሮ ይለውጣሉ።**
- **ዐ/ሕግ የቀረው በበቂ ምክንያት መሆኑ መረጋገጥ አለበት- ቁ. 94(2)(ሀ)**

- ምስክር ሳይቀርብ ሲቀር
- ቀጠሮ መለወጥ፤
- አስኪገኝ ማቀረጥ፤
- ምስክሩ የሰጠውን ቃል በማስረጃነት መመርመር
- ቁ. 94(2)(ለ)- ምስክር ሲቀር ቀተሮ ይለወታል፤ ሁኔታዎቹን ግን አይደነግግም፤
- ቁ. 96ን በማገናዘብ መወሰን ያስፈልጋል- ቀጠሮ የሚለወጥባቸውን ምክንያቶች ባህሪ ይጠቁማሉ::

- ምስክር ከቀረ ማንም ሰው ለፍትሕ ዕርዳታ የማድረግ ግዴታውን ስልልተወጣ በወንጀል ይጠቃል ቀ. 448 ይህንኑ መግለጽ ያስፈልጋል።

ተከሳሽ ሲቀርብ

- ክስ ስለመስማት
- ተከሳሰሹ በሳጥን ውስጥ ሲቀርብ ማንነቱ፣ ዕድሜው እና ሥራው መረጋገጥ አለበት ቁ. 128
- ጸታው፣ አድራሻው፣ የትምህርት ደረጃው፣ የቤተሰብ ሁኔታ መመዝገብ አለበት

- ካገሩን በግልጽ ችሎት መስማት
- ሕ.መ. አ. 20(1)
- ለፍትሕ ዋስትና ነው፤
- ታዳሚ ይገመግመዋል፤
- የተከሳሽ መብቶች እንዳይጣበቡ ያግዛል

- በጠበቃ ስለመከራከር
- ተከሳሽ ህግ የማያውቅ ሊሆን ይችላል፤
- ተከሳሽ አቅም ካለው በራሱ፤
- ያለበለዚያ ፍትሕ እንዳይጓደል ፍ/ቤቱ ጠበቃ እንዲቆምለት ሊያዝ ይችላል
- ሕ. መ. አ. 20(5)
- ከጠበቃው ጋር ለመወየት ጊዜ ሊሰጠው ይገባል።

- **በአስተርጓሚ ስለመታገዝ**
- **ቋንቋውን የማያውቅ ከሆነ አስተርጓሚ ሊመደብለት ይገባል- ሕ.መ. አ. 20(7)፣ የወ.ሥ.ሥ.ቁትር 126(2)**
- **በዕውነት ለማስርጎም መማል አለበት**

ክስን ስለመቃወምና በመቃወሚያ ላይ ስለመወሰን

- ክሱ ተነቦለት እንዲረዳው ከተደረገ በኃላ ይቃወም እንደጀሆነ ፍ/ቤቱ ይጠይቀዋል።
- መቃወሚያ
- 1) በክሱ ፎርም እና ይዘት ላይ ቁ. 130(1)
- በቁ. 111 እና 112ን ይመለከታል፤
- ክሱ ግልጽ መሆን በቁ. 111 የተጠቀሱን ነጥቦች ማካተት አለበት
- ወንጀሉን በዝርዝር መግለጽ አለበት- ቁ. 112

- 2) በቁ. 130 (2) የተመለከተው-
- አብዛኛዎቹ በተከሳሹ የሚነሱ ናቸው
- ቁ.130(2)(ሐ)- የይርጋ ጥያቄ ዐ/ሕጉ ወይም ፍ/ቤቱ ሊያነሳው ይችላል- ፍ/ቤቱ ክሱን መዝጋት አለበት (የወ/ሕ/ ቁ. 216(2)

- የተከሳሹን ፍጽም ወይም ከፊል ኃላፊነት በተመለከተ ምርመራ እንዲደረግ፣ እንዲሁም ስለጠባዩ፣ ያለፈ ታሪኩ እንዲመረመር ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል [ወ/ሕ/ቁ. 51]
- ተቃውሞ የሚቀርበው መቼ ነው
- ክሱ እንደተነበበ ወዲያውኑ
- በጊላ ማንሳት አይችልም [ቁ. 130(3)]

- ዘግይቶም ሊያነሳ የሚችለው
- ከዚህ በፊት ተከስሶ ተወስኖ ከሆነ- ቁ. 130 (2)(ለ)፣ ሕ.መ. አ. 23
- በይርጋ የታገደ፣ ምሕረት፣ ይቅርታ የተደረገለት ከሆነ- ቁ. 130 (2)(ሐ)፣ ሕ/መ/አ. 71(7)
- ለድርጊቱ ኃላፊ ካልሆነ - ቁ. 130 (2)(ሰ)

- መቃወሚያ በቃል መቅረብ አለበት- ቁ. 130(1) (2)፣ 131 (1)

- ሌሎች መቃወሚያ ምክንያቶችስ?
- አንዳንዶች- በቀ.130 ላይ ባይሸፈንም ሌሎች ምክንያቶችም ሊቀርቡ ይገባል፤
- ሌሎች- ሌላ መቃወሚያ ነጥብ በማይጨምር መልኩ ነው ቁ. 130 የዘረዘረው ይላሉ።

- **በመቃወሚያ ላይ ስለመወሰን**
- **ፍ/ቤቱ መቃወሚያውን በመጻፍ ዐ/ሕጉን አስተያየት ይጠይቃል**
- **ፍ/ቤቱ ወዲያውኑ ይወስናል።** [የወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/131(1)]
- **ለመወሰን ማስረጃ መቅረብ ካለበት ማስረጃው እንዲቀርብ ፍ/ቤቱ ሊያዝ ይችላል**[የወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/131 (3)]
- **ማስረጃውን ሰምቶ ወዲያውኑ ይወስናል** [የወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/131(4)]

- ውሳኔውም በዋናነት በቁ. 130 በተደነገገው መሠረት ይሆናል።

ክስን ስለማሻሻል እና ክስን ማንሳት

- ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት- በራሱ አስተያየት ወይም በባለጉዳዮች አመልካችነት ክስ እንዲሻሻል ሊያዝ ይችላል ቁ/ 119
- ዋና ስህተት ሲገኝ፣ ተከሳሹን የሚያሳስት ወይም ያሳሳተ በመሰለ ጊዜ
- የማሻሻል ዓላማ ምንድነው?
- አከራካሪ ነው

- ለተከሳሹ ጥቅም ሲባል፣ ቁ. 119
- ለትክክለኛ ፍትሕ ሲባል ቁ. 118 እና 119
- ውጤቱ- ቁ. 120 እና 121
- የተሻሻለው ክስ ሲቀርብ ለተከሳሹ እንዲደርሰው ተደርጎ ሂደቱ እንደ አዲስ ይጀምራል
- ዐ/ሕግ ማስረጃውን ያሰማል፣ ተከሳሽም መከላከያውን ያቀርባል

- **ክስ ስለማንሳት**
- **ዐ/ሕግ ክስ የማንሳት ሥልጣን አለው -ፍ/ቤት ክስን ስለማንሳት መመርመር አለበትን?**

የመወያያ ጥያቄዎች

- የሰ/ሰ/ች/መ/ቁጥር 46412
- 1) በማስረጃ የተረጋገጠው ዐ/ሕግ ካቀረበው ክስ ያነሰ ሆኖ ሲገኝ ፍ/ቤቱ ምን ማድረግ እንዳለበት ከጉዳዩ ጋር በማገናዘብ ያብራሩ::
- 2) የፍ/ቤቱን ውሳኔ ስለወጣት ጥፋተኛ በሕጉ ከተደነገገው አንጻር ይገምግሙት::
- 3) በፍ/ቤቱ ውሳኔ ትስማማላችሁን? ለምን?

የመወያያ ጥያቄዎች

- የሰ/ስ/ች/መ/ቁጥር 57632
- 1) ተጠሪ በሌለበት ይግባኝ መስማት አግባብ ስለመሆን አለመሆኑ ጉዳዩን ከሕግ አንጻር መርምሩት::
- 2) የወንጀል ክስ ማሻሻል የሚቻልባቸውን ምክንያቶች እና መቸ መሻሻል እንዳለበት ጉዳዩን ከሕጉ አንጻር ገምግሙት::
- 3) በወንጀል ጉዳይ አንድን ተከሳሽ ጥፋተኛ ለማስባል ማስረጃው እስከምን ድረስ ማስረዳት እንዳለበት ጉዳዩን ከሕግ አንጻር ገምግሙት::

ዕምነት ክህደት ስለመስጠት

- ስለዕምነት ቃል
- ዐ/ሕግ እና ተከሳሽ የሚያደርጉት ስምምነት በተከሳሽ የሚሰጥ የእምነት ቃል
- ክስ ከተሰማ በኋላ የሚሰጠው የዕምነት ቃል
- ፍ/ቤቱ የክሱን ዝርዝር ለተከሳሹ ማስረዳት አለበት፤ (ቁ. 132(1) እና ሕገ.መ. አ. 20(2))
- የወንጀሉን የሕግ፣ የሞራል እና ግዙፋዊ ተግባሮች ማስረዳት (ቁ/111(1)(ለ) እና የወ/ሕ/ቁ/23)

- ፍ/ቤቱ የተከሳሹን እምነት ከተጣራጠረ- ዐ/ሕግ ማስረጃ እንዲያቀርብ ሊፈቅድ ይችላል ቁ/134(2)
- ወይም የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠት (ቁ/134(1))

ስለክህደት ቃል

- የክህደት ቃል ሰጠ የሚባለው በቁ. 133 (1) ተከሳሹ
- መልስ ያልሰጠ እንደሆነ፣
- ወንጀሉን አልፈጸምኩም፣ ጥፋተኛ አይደለሁም ካለ፤
- ወንጀሉን አምኖ ስለአፈጻጸሙ ምክንያት ከሰጠ፣(ቁ. 133(2))

ስለዕምነት ክህደት መለወጥ

- የዕምነት ቃል ማሻሻል ይቻላል- ቁ/ 135
- የዕምነት ቃል ለማሻሻል ሁኔታዎች ወይም ምክንያቶች በሕጉ አልሰፈሩም
- መቼ
- ክህደት ከተመዘገበበት እስከ የጥፋተኛነት ውሳኔ እስከተሰጠበት ባለው ጊዜ ቁ/135 (1) (2)

4) ማስረጃ አቀራረብ እና ቀጠሮ

- 1)ምስክሮች ካልቀረቡ ወይም ካልተሟሉ
- ምስክሮች ሳይቀርቡ ከቀሩ ቀጠሮ መለወጥ- ቁ. 94(2)(ለ)
- ያልቀረበው ምስክር ተይዞ እንዲቀርብ ቁ/96(1)
- ይዞ የማቅረብ ሥርዓት ቁ/ 125
- ምስክሮች ካልተሟሉ
- አንዳንድ ፍ/ቤቶች አንሰማም በማለት ቀጠሮ ሲለውጡ፣ ሌሎች ደግሞ የቀረበን ምስክር ይሰማሉ

- ኤግዚቢት ላይቀርብ ይችላል፤ በፍ/ቤትም ውሳኔ ላይሰጥበት ይችላል

2) ምስክሮችን ስለመስማት

- የዐ/ህግ ምስክር -ክስ ሲሰማ- ዕውነቱን ለማውጣት
- ከሳሽ እንደክሱ ማስረዳት ያለበት

➢ተጠርጣሪ እንደንጹህ ስለሚታሰብ፣

➢ንጹህ ሰው እንዳይቀጣ፣

➢አንዱ ጥፋተኛ ከተባለ እና ከተቀጣ ማስተካከል ስለሚያስቸግር

ስለጭብጥ

- ዐ/ህግ ክስ ከማሰማቱ በፊት ክሱን እና ያቀረበውን ማስረጃ ዓይነት በአጭሩ በመግለጽ ክሱን መክፈት አለበት::ቁ/136 (1)
- ይህም በተለምዶ ጭብጥ ይባላል
- በቁ/124 መሠረት ዐ/ህግ የዘረዘራቸው ምስክሮች ይሰማሉ፤
- ሌሎች ካሉ ፍ/ቤቱ ምስክርነታቸው ለነገሩ አስፈላጊ ከሆነ ሌሎቹ ምስክሮች ተሰምተው ካበቁ በኋላ በፍ/ቤት ትዕዛዝ ሊቀርቡ ይችላሉ::

- ምስክሮች መማል አለባቸው
- ዕውነትን ያለመናገር፣ ሐሠት መናገር በወንጀል ያስቀጣል- ወ/ሕ/ቁ/ 453
- ፍ/ቤቱ የምስክሩን ሥም፣ አድራሻ፣ ሥራውን እና ዕድሜውን፣ ስለመማሉ መመዝገብ አለበት ቁ/147(1)
- ጸብ ወይም ዝምድና እንዳለው መመዝገብ- ለማስረጃው ክብደት ለመስጠት ይረዳል።

- ዋና ጥያቄ- ምስክሮችን ዐ/ህግ መስቀለኛ ጥያቄ መጠየቅ አይችልም ቁ/137 (1)(2)
- ድጋሚ ጥያቄ
- በመስቀለኛ ጥያቄ የነሳውን ነጥብ ለማብራራት ብቻ ቁ/139
- አዲስ ነገር ማንሳት አይቻልም

- የቀድሞ ጥፋተኝነት ሪኮርድ የሚመለከት ጥያቄ ማንሳት አይቻልም
- ፍ/ቤቱ ምስክሩን መመርመር ይችላል
- እያንዳንዱ ቃል በምስክሩ አገላለጽ መመዝገብ አለበት ቁ/147(3)(4)
- የሚመዘገበው ቃሉ እንጂ ጥያቄው አይደለም

- **የዐ/ህግ ማስረጃ እንደክሱ ባላስረዳ ጊዜ**
- **ተከሻሹን ጥፋተኛ ሊያደርገው የማይችል ከሆነ ተከሳሹ በነጻ እንዲለቀቅ ፍ/ቤቱ ያዛል ቁ/141**

- **የዐ/ሕግ ማስረጃ እንደክሱ ባስረዳ ጊዜ**
- **የዐ/ሕግ ማስረጃ በቂ ሲሆንና የማፍረሻ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር ተከሳሹን ጥፋተኛ የሚያደርግ መሆኑን ፍ/ቤቱ ሲያምን- ተከሳሹ መከላከያውን እንዲያቀርብ ፍ/ቤቱ ይነግረዋል -ቁ/ 142(1)**

ስለመከላከያ ማስረጃ

- የመከላከል መብት- ሕ/መ/አ/ 20(4)
- ተከሳሹ በመከላከያ ሊያስረዳ ያቀረበውን ማስረጃ በአጭሩ በመጥቀስ መከላከያውን ማሰማት ይጀምራል -ቁ/142 (2)
- ምስክር መማል አለበት
- በ124 መሠረት የቀረበው ዝርዝር ቁ/124
- በዝርዝሩ ያልተጠቀሰ- እንዲቀርብ ፍ/ቤቱ ሊያዝ ይችላል ቁ/143(2)

- ተከሳሹ ቃሉን መስጠት ከፈለገ- በመጀመሪያ ይሰጣል- ቁ/121
- መስቀለኛ ጥያቄ አይጠየቅም፤
- ፍ/ቤቱ ነገሩን ለመብራራት መጠየቅ ይችላል ቁ/143(3)
- ከዚያም ፍ/ቤቱ ክሱ ተስተባብሎ እንደሆነ ይመረምራል

- ክሱን ከአስተባበለ- ከክሱ በነጻ ይሰናበት፤
- ክሱን አላስተባበለም- ለወንጀሉ ጥፋተኛ ነው

3) በማስረጃ መስማት ጊዜ የፍ/ቤት ሚና

- ሀ) ምስክሮችን መመርመር
- ለትክክለኛ ፍትህ ሲባል በማንኛውም ጊዜ ምስክሮችን ማንኛውንም ጥያቄ ለጠየቅ ይችላል ቁ/136(4)
- ለ) ተጨማሪ ምስክር እንዲቀርብ ማዘዝ
- 1) ለትክክለኛ ፍርድ ፍርድ በመስጠቱ በፊት ምስክር መጥራት ቁ/143(1)
- 2) በዝርዝር ያልተጠቀሰ ምስክር መጥራት ቁ/143(2)

- 3) ተከሳሹ የዕምነት ቃል ቢሰጥም አስፈላጊ ሲሆን ዐ/ሕግ ማስረጃ እንዲያቀርብ ማዘዝ ቁ/134(2)
- 4) በይግባኝ ጊዜ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ የማዘዝ ሥልጣን አለው ቁ/194

- ጥያቄ
- የፍ/ቤት ሥልጣን በግልጽ መደንገግ አለበትን?

4) የክርክር ማቆሚያ ንግግር

- የክርክር ማቆሚያ ንግግር/የመፋረጃ ሃሳብ)
- በቃል መቅረብ አለበት- በተግባር ግን በጽሑፍ ሲቀርብ ይታያል
- መጀመሪያ ዐ/ሕግ ቀጥሎ ተከሳሽ ይናገራሉ።

ስለወጣት አጥፊዎች ወንጀል ሥነ ሥርዓት

- ሕጻን ማለት- ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ማናቸውም ሰው ነው [የሕጻናት መብቶች ኮንቬንሽን አ. 1፣ አሕመደቻ አ. 2፣ የቤተሰብ ሕግ አ. 215]
- የወንጀል ተጠያቂነት ዕድሜ በየሀገሩ የተለያየ ነው::
- በኢትዮጵያ- 9 ዓመት [የወ/ሕ/ቁ. 53]

- ወጣት አጥፊዎች የሚባሉት ከ9-15 ዓመት ያሉ ሕጻናት
- ከ15-18 ዓመት ላሉ ሕጻናት ጥበቃ የሚደረገው ከጥፋተኝነት ውሳኔ በኋላ በቅጣት ጊዜ ነው። [ወ/ሕ/ቁ. 56]
- ከወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/171- 180 -ያሉት ድንጋጌዎች ይተገበራሉ።

የክስ አጀማመርና የወንጀል ምርመራ ሂደት

- መታየት ያለበት ለችግሩ የዳረጋቸው ምክንያት ነው::
- ዓላማው ቅጣት ሳይሆን የወደፊት ሕይወታቸው ፈር የሚይዝበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው::
- የፍትሕ ዓላላት እንደሐኪም ችግራቸውን ማከም ነው ያለባቸው::
- የሕጻናቱን ችግር ለመረዳት የሥነልቦና እና የማህበራዊ ሣይንስ ባለሙያ ዕርዳታ ያስፈልጋል::

- በአ.አ. ፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በሕጻናት ጉዳይ ባለሙያዎችን የማሳተፍ አሠራር ይተገበራል።

የወጣት አጥፊዎች የፍርድ ሂደት

- ዐ/ሕግ በከፍተኛ ፍ/ቤት በሚቀርቡ ጉዳዮችን መከታተል አለበት- ቁ/176።
- ክርክሮች
- ሀ) ዐ/ሕግ ክሱን ካዘጋጀ መከታተል አለበት፤
- ለ) ጉዳዩን በችሎት የመከታተል መብት የለውም፤
- የሕጻን ወላጅ፣ ሞግዚት፣ አሣዳሪ ወይም ቤተዘመድ ይቀርባል፤
- ከ10 ዓመት በላይ ጽኑ እሥራት ወይም በሞት የሚጠጠስቀጣ ወንጀል ሲሆን ፍ/ቤቱ የግድ ጠበቃ እንዲቆምለት ማድረግ አለበት።

- መዝገቡ ከተቀጠረ፣ ሕጻኑ በአደራ ለወላጅ፣ ዘመድ ወይም ተቋም መሰጠት አለበት።
- አደራ ተቀባዩ ዋስትና ስለመስጠት አልተደነገገም፤
- በሂደቱ ሕጻኑ ሊሰማው የማይገባው ነገር ካለ ከችሎት ይወጣል።
- በዝግ ችሎት መታየት አለበት። [ወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/176]

- ክሱ ሲሰማ መቃወሚያ ጭምር መቅረብ አለበት።
- ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ሊሻሻል ይችላል።
- ሕጻኑ በሌለበት ክሱ ሊስተናገድ አይችልም [ወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/160]
- ምስክሮች የሚመረመሩት በፍ/ቤቱ ነው።
- በተከሳሽ ወገን ብቻ የማቆሚያ ንግግር ይደረጋል።
- ከዚያም ፍ/ቤቱ ፍርድ ይሰጣል።

የወንጀል ተጠቂዎች መብቶች

- የፍትሕ ተደራሽነት- ለአጥፊም ለተጠቂም ነው [ወ/ሕ/ቁ.1]
- ተጠቂ ማነው?
- ማህበረሰቡ በጥቅል- ሠላማዊ ሕይወቱ ይናጋል፣
- ቀጥተኛ የወንጀል ሰለባ የሆነው- የግል ተበዳይ ወይም የግል ተበዳይ ቤተሰቦች
- የወንጀል ተጠቂዎች ተጠርጣሪን ለፍርድ እንዲቀርብ የማድረግ መብት አላቸው::

1) በክስ ሂደት የመሳተፍ መብት

- ተጠቂው ተጠርጣሪውን ለፍርድ ማቅረብ ይፈልጋል።
- ይህን ለማሳካት በሂደቱ እንዲሳተፍ በማድረግ ጥቅሙን ወይም ፍላጎቱን ማስከበር ነው።
- ተጠቂው የመደመጥ መብቱን የሚመለከት ነው።
- ተጠቂ የሥነልቦና እና ማህበራዊ ጠባሳ ስለሚገጥመው መደመጥ አለበት።

- ተጠቂ ሪፖርት በማድረግ ምርመራ እንዲደረግ መብት አለው- [ወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/23]
- ተጠርጣሪው ዋስትና ቢጠበቅለት ተጨማሪ ጥቃት ሊያደርስ ይችላል።
- ማስረጃ ሊያባክን ይችላል
- በዋስትና ጥያቄ ሂደት ተጠቂው ሊሳተፍ ይገባልን?

- ለወንጀል ክስ ከተጠቂው የበለጠ ምስክር የሚሆን የለም::
- የተጠቂ ምስክርነትን በዝግ ችሎት ማድረግ፤
- በቅጣት ማቅለያና ማከበጃ ሲታይ የወንጀል ተጎጅው የጎላ ሚና ሊኖረው ይችላል

2) የካሳ መብት

- ተጠቂው ለደረሰበት ቁሳዊ፣ ሞራላዊና አካላዊ ጥቃት ካሳ የማግኘት መብት አለው።
- ለመክፈል አቅም ባይኖረውስ?
- ከወንጀለኛው ላይ ከተያዘው ዕቃ ከሚገኘው ገንዘብ፣ መያዣ ካስያዘው ላይ፣ ከመቀጮ፣ በጉልበት ሥራ ተለውጦ
- የመከራከር አቅም ለሌለው ተጠቂ ዐ/ሕግ ሊከራከርለት ይችላል

ይግባኝ

- ይግባኝ - አንድ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለትን የወንጀል ክስ በማቋረጥ ተከሳሹን ለጊዜው በመልቀቅ በሚሰጠው ትዕዛዝ፣ ወይም የቀረበለትን የወንጀል ክስ ከሕጉና ከማስረጃ ጋር አገናዝቦ በሚሰጠው የመጨረሻ ፍርድ ላይ ቅሬታ ያለው ሰው ቅሬታውን ለበላዩ ፍ/ቤት አቅርቦ የተሰጠውን ትዕዛዝ/ፍርድ **ትክክለኛነት** የሚያስመረምርበት ሂደት ነው::

- ይግባኝ ያስፈለገባቸው ምክንያቶች
- ሀ) ስህተቶችን ለማረም
- የተሻለ የትምህርት ዝግጅት፣ የሥራ ልምድ እና ክሂሎት ባላቸው የበላይ ፍርድ ቤት ዳኞች ስህተት አለበት የተባለውን ፍርድ ማየትና ማረም ያስፈልጋል።

- ለ) **ቁጥጥር ማድረግ**
- የይግባኝ ሥርዓት ፍርድ እንዲመረመር ያደርጋል፤ ይህም ዳኛው ይመዘንበታል፤ ዕድገት ያገኝበታል፤ ወይም ይወቀስበታል።
- ዳኛውም የበላይ ፍ/ቤት መልካም ግምትን ለማግኘት በተቻለ መጠን ሥህተቶች እንዳይኖሩ ለማድረግ ይጥራል።

የይግባኝ መብትና ወሰኑ

- ይግባኝ ሕገመንግሥታዊ መብት ነው- (አ. 20(6))
- ወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/184- በትዕዛዝ ላይ ይግባኝ አይባልም፤
- በዋናው ጉዳይ ላይ ይግባኝ ሲባል ተጠቃለው ሊቀርቡና ሊታዩ ይችላሉ::

- ይግባኝ የሚባልባቸው (ወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/185)

➢በጥፋተኝነትና በቅጣት ውሳኔ፤

➢በዕምነት በተሰጠ ፍርድ **በቅጣቱ** ላይ ብቻ፤

➢ለጊዜው በመልቀቅ፣ ነጻ በመልቀቅ እና በቅጣቱ መጠን ላይ

ስለይግባኝ ጊዜ

- ፍርድ በተሰጠ በ15 ቀን ውስጥ ይግባኝ ለማቅረብ እንደሚፈልግ በመግለጽ ፍርዱን ለሰጠው ፍ/ቤት የይግባኝ ማስታወቂያ አቤቱታ ማቅረብ፤
- ማስታወቂያው የደረሰው ፍ/ቤት ሬጅስትራር ፍርዱን አስገልብጦ ይሰጠዋል፤
- ግልባጭ በደረሰው በ30 ቀን ውስጥ ቅሬታውን አዘጋጅቶ ፍርዱን ለሰጠው ፍ/ቤት ሬጅስትራር ማቅረብ አለበት::

- ፍርዱ ደረሰ የሚባለው ማረሚያ ቤት ላለ ሰው ወይስ ለማረሚያ ቤቱ ሲደርስ ነው?
- የፍርድ ግልባጩ ለማረሚያ ቤት የደረሰበት ቀንን ሕጉ የመረጠ ይመስላል- ቁ/187 (1)

የይግባኝ ክርክርና ውሳኔ

- ይግባኝ ክርክር በቃል መደረግ ይገባዋል- ቁ/192
- የግራ ቀኙ ክርክር በአንድ ቀጠሮ የሚጠናቀቅ ነው::
- በተግባር- በጽሑፍ ክርክር ይቀርባል::
- በሕግ ተለይተው ከተገለጹ ወንጀሎች ውጭ ተከሳሽ በሌለበት ሊታይ ይችላል- ቁ/193(2)::
- ተጨማሪ ማስረጃ ካስፈለገ- ፍ/ቤቱ ምክንያቱን ጽፎ ማስረጃውን ሊቀበል ይችላል- ቁ/ 194

- **ውሳኔ**

➢ **በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን የጥፋተኝነትና ቅጣት ውሳኔ መሠረዝ፤**

➢ **የጥፋተኝነት ውሳኔ በማጽናት ቅጣት መቀነስ፤ ወይም**

➢ **በሥር ፍ/ቤት በነጻ የተለቀቀን ተከሳሽ ጥፋተኛ በማድረግ መቅጣት፤**

- ጉዳዩ ወደሥር ፍ/ቤት ተመልሶ እንደገና እንዲታይ ማዘዝ ይቻላል- ቁ/ 195
- ቅጣት በዛብኝ የሚል ይግባኝ ሲቀርብ መጨመር ባልተጠየቀ ዳኝነት መፍረድ ስለሚሆን ተገቢ አይደለም::

- አመሰግናለሁ!!!